# የኢትዮጵያ ህዝብ የገባበት አጣብቂኝ መነሻው፣ መዘዙና መፍትሄው

*እስክ ነጻነት*

ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ በመሪ ሳንተዳደር በገዥዎች ቀንበር ተጠምደን ስንማቅቅ ብዙ፣ በጣም ብዙ ጊዜ ያለፈን መሆኑን መናገር ለቀባሪ ማርዳት ስለሆነ መዘርዘር አያስፈልግም: የአስተዳደር ስርአታችን ምህዋሩን ለቆ መጓዝ ከጀመረ ብዙ አስርተ አመታት አልፈዋል: ይህም የሐገሪቷ ምህዋር መልቀቅ የሚያሳስባቸው፣ የሚያስጨንቃቸው ዜጎች አቅጣጫውን ለመቀየርና ወደ ተገቢው ተፈጥሯዊ የአስተዳደር ምህዋር ለመመለስ ደፋ ቀና ማለታቸው የማይካድ ሐቅ ነው: ወደ ምህዋሩ መመለስ የምችለው "እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ" በሚል ሁሉም የበኩሉን ሐሳብና እቅድ ነድፎ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከሚደረገው እሽቅድምድም በተጨማሪ *አንቱ ለመባል ስምና ዝናን ለማትረፍ ንብረትም ለማካበት አጋጣሚውን ለመጠቀም የሚራወጡ ቁጥራቸው ቀላል እንዳልሆነም እንገነዘባለን::*
እስከ አሁኗ ደቂቃ ድረስ ግን እንኳን ለውጤት ያበቃ ቀርቶ የተቃረበ እንኳ ለማየት አልታደልንም: በ1997 ምርጫ ለውጤት ተቃርበን ነበር ግን በመሪ ማጣት ወጤቱን ድሉን ተነጥቀን እንደ ገና ለዳግም ባርነት ተዳርገናል::
ለመሆኑ ይኽ ሁሉ ድርጅት እያለና ይኽ ሁሉ ጥረት እየተደረገ ለውጤት ያልበቃነው ለምንድነው? የሚለው ጥይቄ የሁላችንም ነው ብዬ አምናለሁ:

የችግሩ ምንጭ እንደኔ እምነት ከሆነ **የመጀመሪያው** ለመሪ ያለን እይታና ግንዛቤ ሲሆን፣ **ሁለተኛው** ደግሞ የሐገሪቷ የጂኦግራፊ አቀማመጥ የሩቅና የቅርብ ጠላቶችችን የሚስብ መሆኑ ይመስለኛል: ሰለሁለተኛው ምክንያት አሁን ልለፈውና ስል አንደኛው ሰለ መሪ ችግር በዚህ ጽሑፌ ለመዳሰስ እሞክራለሁ::

ስለመሪ ያለን ግንዛቤ መሪ ነን ብለው ራሳቸውን በሚያቀርቡትም ሆነ ተመሪ ነን ብለን በምንከተላቸው ህዝቦች በኩል እኩል የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳለ ይታየኛል: በመጀምሪያ ግለሰብ መሪ በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን ማስረዳት ያለብኝ አይመስለኝም: ያለ ግለሰብ መሪነት ምንም እንቅስቃሴም ሆነ ውጤት ሊገኝ አይችልም: **ትክክለኛ** መሪ በፍርሃት ቆፈን የተጨማደደን፣ ዙሪያው ገደል ሆኖበት ተስፋ የቆረጠን ህዝብ ወደ ፍርሃት አልባ ጀግና፣ ልበ ሙሉ አልደፈር፣ አልገብር ባይነትና ብሩህ ተስፋ አላሚነት መቀየር የሚችል አካል ነው: አንድ ምሁር የትክክለኛ መሪን አስፈላጊነት ሲገልጹ እንዲህ አስቀምጠውታል: እጠቅሳለሁ ***"በአንበሳ የሚመራ የበጎች ሰራዊት ሁልጊዜም በበግ የሚመራ የአንበሶች ሰራዊትን ያሸንፋል"*** መሪ ተብዬው በግ ለአንበሳው ሰራዊት የሚያስተላልፈው መልእክት የፍርሃት፣ የመሸነፍ የመደንገጥ እና አቅልን አላማን ግብን የመሳት መልእክት ነው: በዚህም ምክንያት ወደ ጦርነቱ ሲገቡ መሸነፋቸውን አምነው ስለሚሆን ውጤቱም የጠበቁት ይሆናል: በአንጻሩ የበጎቹ መሪ አንበሳው ደግሞ ለበጎቹ የሚያስተላልፈው መልእክት የድፍረት የአሸናፊነት፣ የድል አድራጊነት ስለሆነ የበጎቹ ሰራዊት ወደ ጦርነቱ ሲገቡ በሙሉ ልብ ድል አድራጊነት ስለሚሆን እንደ ሓሳባቸው ይፈጸማል:

*መሪነት ጥበብ ነው: መሪነት እንደ ሰዓሊነት፣ ደራሲነት የሚታደሉት ተሰጦ እንጂ እስኪ ልሞክረው ተብሎ የሚገባበት የስራ ድርሻ አይደለም: መሪነት በትምህርት፣ በዘር፣ በአካል ብቃት ወይም በሐብት ብዛት የሚገኝ አይደለም: መሪነት በውስጥ ማንነት የሚገለጥ፣ የተፈሮ የአመራር ችሎታ የሚታከልበት፣ ያም ደግሞ በትምህርትና በምርምር፣ በልምድ የሚዳብር የጥበብ ዘርፍ ነው:*
ምንም እንኳ መሪነት በተፍጥሮ ለሁሉም የሰው ልጆች የተሰጠ ጸጋ ቢሆንም ከውስጥ ፈንቅሎ የሚወጣው ግን በተውሰኑ ሰዎች ዘንድ ብቻ ነው: እንደዚያ ባይሆን ኖሮማ እስካሁን መሪ ነን እያሉ ስንት የፖለቲካ ድርጅት ያቋቋሙ ሁሉ ለመሪነት ስልጣን በበቁ ነበር: መሪ ከተከታዮች የተለየ አስተሳሰብ ባህሪይ (attitude) ያለው/ላት ሰውን የማሳመንና በዙሪያው ለማሰለፍ ብቃትና ችሎታ ያለው ነው/ነች:

ትክክለኛ መሪ ልክ ሰዓሊ የሚስለውን ስዕል ሸራው ላይ ከማሳረፉ በፊት በአእምሮው ያለቀ፣ የተጠናቀቀ ቅርጽ እንደሚታየው ሁሉ መረም በአእምሮው ተቀርጾ የሚታየው የተሻለች አገር፣ የኑሮ ደረጃው ከፍ ያለ ህዝብ፣ ከበሽታ፣ ከጉስቁልና፣ ከመሃይምነት የተላቀቀ ህዝብ፣ ህጻናት በፍራቻ ሳይሆን በደስታ የሚቧርቁባት ሐገር የፍርድ ስርአቱ የተስተካከለባት፣ የህዝቦች መብት ጥያቄ ውስጥ የማይገባባት፣ ህዝቧ ዛሬን ምን ልብላ ሳይሆን ለተተኪ ትውልድ ምን አፍርቼ ልለፍ የሚልባት ሐገር ሰው በዘሩ፣ በቋንቋው፣ በኃይማኖቱ፣ በቆዳው ቀለም ሳይሆን በሰብአዊ ፍጡርነቱ ብቻ የሚከበርባት፣ በዓለም አቀፍ መድረክ የችግር፣ የረሃብ፣ የቸነፈር፣ የበሽታ፣ የድንቁርና ተምሳሌት

ሳይሆን የእድገት፣ የብልጽግና፣ የባለታሪክነት፣ የተስተካከለ አመራር ተምሳሌት የምትሆን አገር ምስል ነው:

**መሪነት** እንደ ማንኛውም የጥበብ ዘርፍ ልክፍት ነው: ትክክለኛ መሪን ገንዘብ፣ ጥሩ ኑሮ፣ ድሎት፣ ስምና ዝና አያረካውም: የሚያረካው ህልሙ፣ ራዕዩ እውን መሆን ሲችል ብቻ ነው:

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ሁሉም ተነስቶ ከጭንቀት ወይም ከተለየ ዓላማ በመነሳት፣ እኔ ልምራችሁ ተከተሉኝ ብሎ የሚነሳው መሪ ሁሉ ይህ ተሰጦ ስላልነበረው፣ ስለሌለው የመሪነት ብቃቱን ራሱ እንኳ ሳያምንበት እየገባበት ለቁም ነገር ሳይበቃ እንደ ዋለለ ቀርቷል: እኛም ልምራችሁ ብሎ የተነሳ ሁሉ መሪ የሚሆን እየመሰለን ስንከተል ገደል አፋፍ ላይ እያደረሱን እንኳን እኛን ሊመሩ ቀርቶ እነሱም አቅጣጫው ጠፍቶባቸው የሞት የሽረታቸውን ሲንደፋደፉና ጠላት ጎራ ሲመሰጉ በተደጋጋሚ አይተናል::

*መሪ ነኝ ያለ ሁሉ መሪ አይደለም አይሆንምም::*

ሌላው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሪ ነኝ ባይ እንዲመለክ እንዲሰገድለት ሰው ሁሉ እንዲሽቆጠቆጥለት ይፈልጋል: እኛም ተመሪዎች ወይም ተከታዮች መሪዎችን እንደ ተለዩ ፍጡሮች የማየት፣ አላግባብ የማክበር ጎንበስ ቀና በማለት ባህል ተጠፍረን የተያዝን ነን: **መሪ በመሰረቱ ለህዝብ አገልጋይ እንጂ በህዝብ ተገልጋይ አይደለም መሆንም የለበትም:** ስለዚህ መሪ መባል ያለበት አንተ ወይም አንቺ ነው: ወደ ስልጣን ከሚያደርገው ጉዞ ጀምሮ በስልጣን ላይም እያለ ህልውናው የሚቆመው በኛ በዜጎች ወይም በተከታዮች የህይወት፣ የጉልበት፣ የእውቀት እና የገንዘብ መስዋእትነት ስለሆነ፣ አመራሩም ካልጣመን ልናስወግደው የምንችለው እኛው ህዝቦቹ ስለሆንን፣ እርሶ፣ አንቱ መባል ያለብን እኛ ነን/ሕዝቦች/ እንጂ መሪዎች አይደሉም: አገልጋያችንን አንቱ ማለት አስፈላጊ አይደለም: እርሶ ካልተባልኩ የመሪነት ስልጣን አልፈልግም የሚል ካለ በኔ በኩል በደስታ እቀበለዋለሁ: እኔ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ መሪ ነኝ ብሎ የሚነሳን ሁሉ አንተ/አንቺ ብዬ የምጠራው መሆኔን ውድ አንባቢዎቼ እንድታውቁልኝ እጠይቃለሁ: ይህን ስል እንኳን ታላላቆቼን፣ ባለስልጣናትን ቀርቶ ወላጅ አባቴን እንኳ አንቱ፣ እርሶ ብዬ ያደግሁ ሰው አሁን ተነስቼ መሪዎቼን አንተ/አንቺ ብዬ መጥራት ምን ያህል ስቅቅ እንደሚያደርገኝ ሳልገልጽላችሁ ማለፍ አልፈልግም: ነገር ግን መሆን ያለበት ነው ብዬ ስለማምን ባህላዊ ግርዶሼን ቀድጄ ጥየዋለሁ: አብሮት የነበረውን የባህል ዲሪቶ ሁሉ አውልቄ መጣል ብቻ ሳይሆን አቃጥየዋለሁ: ተመልሼ ልደርበው ብል እንኳ የለም አላገኘውም: እመራሃለሁና ተከተለኝ ብሎ የተነሳን/ችን ለመከተል ፈቃደኝነቴን ወይም አክብሮቴን ከመቸሬ በፊት ትክክለኛ የመሪነት ብቃት ያለው ያላት መሆኑን ማጣራት ተቀዳሚ ስራዬ ይሆናል::

*ለመሆኑ ትክክለኛ መሪ በምን ይገለጻል፧ ወይም በምን ይለያል?*

ትክክለኛ መሪ የተለዩ ስነ አእምሮ (attitude) ያለው ነው

1. ትክክለኛ መሪ በራሱ የአመራር ችሎታ የሚተማመን፣ ደፋር፣ ለበ ሙሉ፣ የሚታየው ሽንፈት ሳይሆን **ድል**፣ ውድቀት ሳይሆን **ስኬት**፣ ጨለምተኝነት ሳይሆን **ብሩህነት**፧ ጥላቻ ሳይሆን **ፍቅር**፣ በቀል ሳይሆን **በፍትህ ላይ የተመሰረት ይቅር ባይነት ነው:**
2. ትክክለኛ መሪ እንደ ሀውልት የጸና ባህሪይ የሚታይበት ነው: ሐውልት በዝናብ በፀሐይ፣ በብርድ በሙቀት፣ በብርሃን በጨለማ እንደማይቀያየር ሁሉ የመሪ በህሪም እንደዚሁ በድልና በሽንፈት፣ በስኬትና በውድቀት፣ ተቀባይነት በማግኘትና በማጣት ጊዜ አይቀያየርም: ባጭሩ በድል፣ በስኬት አይፈነጥዝም፣ በሽንፈት ጊዜ አይሽበርም፣ ተሰፋ አይቆርጥም፣ በተከታዮቹ ተቀባይነቱ በበዛ ጊዜ አይፈነጥዝም፣ ተቀባይነቱ ሲቀንስ አያኮርፍም አይነፋነፍም: አቅሉን አይስትም: በአቋሙ እንደ ጸና ይኖራል::
3. ትክክለኛ መሪ የቀድሞ ስህተቱ ወይም ውድቀቱ በወደፊት ራእዩ ላይ አያጠላበትም ካለፈ ስህተቱ ወይም ውድቀቱ ተመክሮ ወስዶ ለቀጣይ ግቡ በጥንካሬ የሚጓዝ ነው:
4. ትክክለኛ መሪ በቀለኛ፣ ቂመኛ አይደለም **ይቅር ባይ ነው** (forgiveness) እዚህ ላይ ይቅርታ ስል ወንጀለኛ ወንጀሉ ይሰረዝለታል ማለት እንዳልሆነ ልብ ልትሉልኝ ይገባል: ይቅርታ ማለት *በቀልን በራስ እጅ አልመውሰድ ለህግ አሳልፎ መስጠት ማለት ነው: ይቅርታ በጽኑ የህግ ስርአት ላይ እስካልተመሰረተ ደረሰ ዘለቄታ አይኖረውም::*
5. ትክክለኛ መሪ ተከታዮችን በተከታይነት ይዞ የሚጓዝ ሳይሆን ተተኪ መሪዎችን የሚያፈራ ነው:
6. ትክክለኛ መሪ በቅርብ ዕይታ ወይም በዓይነ ሥጋ ዓይን አድማስ አይመራም

ይልቁንም በዓይነ ህሊናው ራዕይ የሚመራ ነው:

7. ትክክለኛ መሪ ለአብዛኛው ህዝብ የኑሮ መሻሻል፣ ለልጅ ልጅ የሚወረስ ቅርስ ለማዘጋጀት፣ ዓይን ከሚያየው ርቆ ለተቀመጠ፣ በዓይነ ህሊና ብቻ *ለሚታይ ራዕይና ግብ ለመድረስ እንደ ንስር አሞራ የሚመነጠቅና ወገኖቹንም ከወደቁበት ዘርፈ-ብዙ አረንቋ መንጥቆ ለማውጣት በራሱ የሚተማመንና የህዝብ አመኔታን ማትረፍ የሚችል ልዩ የአመራር ጸጋ የተቸረው ነው:*
8. ትክክለኛ መሪ የማያምንበትን አይናገርም የተናገረው ቃሉ፣ ቃል ኪዳኑ ነው: **በቃሉ የጸና በእምነቱ የጠነከረ ነው:** ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ለሚያደርገው ጉዞ ችግር፣ እስራት፣ እንግልት፣ ስቃይ አያግደውም: የመንገዱ ጠመዝማዛነት፣ እሾሃማነት፣ ወጣ ገባነት አይገድበውም: እንዳውም የበለጠ ያጠነክረዋል ያጸናዋል:

ትክክለኛ መሪነት እንግዲህ ከላይ ከሞላ ጎደል ከላይ የጠቃቀስኳቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ ግለሰብ ነው::

**በቡድን አመራር ወደ ግብ መቃረብ ይቻላል ለድል ለመብቃት ግን የግድ የተናጠል ወይም የግለሰብ መሪነት ያስፈልጋል:** የ1997 ምርጫም ለመጨንገፍ ካበቁት ምክንያቶች አንዱ ይህ የትክክለኛ መሪ የማጣት ጉዳይ ነው ብዬ አገምታለሁ:: እያንዳንዱ ሰው የራሱ ተሰጦ አለው ሁሉም መሪ አይሆንም ሁሉም ተመሪ አይሆንም: እያንዳንዱ እንደ ተሰጠው ለሐገሩ ለወገኑ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለ: ማንም ሰው ደግሞ ለራሱ  ከሰጠው ግምት ባላይ ሊሄድ አይችልም: እያንዳንዱ የሚደርስበት የኑሮ ደረጃ ለራሱ ብቃት ካለው ግንዛቤ ሊዘል አይችልም: **የያንዳንዱ ግለሰብ ተግባር የስነ ልቦናው ነጸብራቅ ነው:**

በዚሁ መሰረት እያንዳንዱን ፖለቲከኛ ሥነ- ልቦና (mind setup) መመልከትና መተነተን ይቻላል:

ሁሉንም ፖለቲካኛ ነኝ ወይም የፖለቲካ ድርጅት መሪ ነኝ የሚሉትናን በሐገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን (ከሐገር ውጭ ያሉትን በሌላ ጊዜ ስለምመለስበት ነው) መመርመርና መፈረጅ የሚቻል ቢሆንም የአንባቢን ጊዜና የግል አስተሳሰቡንና የአድማስ ገመዱን መገደብ ወይም የሐሳብ አቅጣጫው ላይ ተጽዕኖ ማድረግ እንዳይሆንብኝ፣ አንባቢዎቼ ስለ እያንዳንዱ የፖሊቲካ መሪ የአመራር ብቃት፣ የሐገሪቱን በትረ-ስልጣን ተረክቦ ሊያስተዳድር፣ ህዝቡን ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማሸጋገር ብቃቱ፣ ተሰጠው፣ የስነ ልቦና ዝግጅቱ፣ የተፈጥሮ የአመራር ችሎታው፣ አለው ወይ? ብላችሁ ወደ ራሳችሁ ድምዳሜ እንድትደርሱ ጋብዤ አልፈዋለሁ:

**በኔ በኩል የአመራር ተሰጦ፣ ችሎታ፣ እውቀቱ፣ የሥነ ልቦና ዝግጅቱ፣ ራዕዩ አላት የምላት የሰላም መሪ ከሐግረ ውስጥ አንድ ብርቱካን ሚደቅሳ ብቻ ነች::**

የተቀሩት ሐገራቸውን በተለያየ የሙያና አገልግሎት ዘርፍ የማገልገል ብቃቱና ችሎታው ያላቸው መሆኑን እያመንኩ፣ በዚያም በተሰጣቸው ፀጋ ሐገርና ህዝባቸውን ከማገልገል አልፈው መራሄ መንግስቱን ከመለስ ነጥቆ፣ ተረክቦ ለማስተዳደር ብቃቱ አለው ብዬ የማምነው ግለሰብ ግን የለም

መለስ በካርተር ማእከልና በእንግሊዝ መንግስት የተተከለ የውክልና ገዥ መሆኑን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ጂሚ ካርተር ለኖቬል ሽልማት ያበቃውን የግብጽና የእስራኤል ስምምነት ሲያፈራርም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት መማለጃ ማድረጉ ልብ የማይል ያለ አይመስለኝም: ይህም ወያኔ ወዲያው ስልጣን እንደያዘ እ. አ. አ. 1993 የመጀመሪያውን የሐገር ህልውናና ጥቅም አሳልፎ የሰጠበትን ናይል ፍሬም ወርክ አግሪመንት (Nile Framework Agreement) ከግብጽ ጋር መፈራረሙን ማስታወስ ያስፈልጋል: *መለስ ዜናዊ የቆላ እባብ (የኮብራ) ጭንቅላት ያለው ሰው ነው: አሳቡ ሁሉ አጠገቡ የተገኙትን፣ ለስልጣኑ ያስጋኛል የሚላቸውን አስደንግጦ የማባረር እንዲያም ሲል መርዞ የመግደል ባህሪ ያለው ፍጥረት ነው:* ከአረጋዊ በርሄ ጀምሮ የተባረሩትና አድራሻቸው የጠፉ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች ለዚህ ባህሪው በቂ ምስክር ናቸው: ስልጣን ከያዘ በኋላም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ እልቂት እስከ ትናንቱ የነ ጄነራል ተፈራ ማሞ ፍርድ ድረስ ምን ያህል ህዝብ እንደ ፈጀ ፀሀይ የሞቀው፣ ማወቃቸውን መናገር ባይፈልጉም  ዓለም ያወቀው ጉዳይ ነው::
**የመለስን መርዝ በሰላም የዘምባባ ዝንጣፊ ተከላክላ በህግ ባላ አንገቱን ጠምዝዛ መርዙን ወደራሱ ልታስተፋ የምትችል ብቸኛ ሰው ድግሞ ብርቱካን ነበረች:ይህንን ድግሞ ወያኔ ብቻ ሳይሆን የምዕራብ አጋሮቹ ጠንቅቀው ሰለሚያውቁት፣ አዳኝ ውሻቸው ከስልጣን እንዲባረርባቸው ስለማይፈልጉ ብርቱካን እንድትታሰር ወያኔን መከረዋ የሚል ጽኑ እምነት አልኝ:**

የአንድነት መሪዎችም (የነ ኢንጂነር ግዛቸው ቡድን ማለቴ ነው) መታሰሯን ፈልገውት ነበር ለማለት ባልደፍርም መታሰሯ ግን እንዳላስከፋቸው ጥርጥር የለኝም: ይህም በተለያዩ ጊዜ ከድርጅቱ ቃል አቀባይ ጀምሮ የሰጧቸው ቃለመጠይቆች እሷን ለማስፈታት የሚደረጉ አገም ጠገም እንቅስቃሴዎች ዋቤ ናቸው:

ማጠቃለያ:

- ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ የድርጅት መሪዎች መካከል የመሪነት በትረ መንግስትን ለመረከብና ሐገሪቱናን ህዝቡን ለመምራት የተዘጋጀ፣ ችሎታውና ተሰጦ አለው የምለው ሰው ሐገር ውስጥ አላገኝሁም :
- አንድ መሪ ብትኖር ለጊዜው አካሏ እስር ቤት ነው መንፈሷና ራዕይዋ ግን በዓለም ሁሉ እየተናኘ እየተሰራጨ ነው ይሰራጫልም:
- መለስ ዜናዊ ከዘረኛ አምባገነንነቱ በተጨማሪ የካርተር ማእከልና የእንግሊዝ ተወካይ ባንዳ እንጂ ኢትዮጵያዊ ገዥ አይደለም:
- ኢትዮጵያ በሰላምና በብልጽግና እንድትኖር የማይፈልጉ ዘርፈ ብዙ ጠላቶች ያላት ሐገር ነች: ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ ደግሞ አሁን ሁኔታዎች ሁሉ ተመቻችቶላቸዋል:
- ከአንድነት ድርጅት ቃርመን ልናስቀር የምንችለው አላማውን፣ ህገ ደንቡን፣ ህዝቡንና ብርቱካንን ብቻ ነው የሚል ጽኑ እምነት አለኝ:
- ከዚህ ሌላ ነጻ ሊያወጣኝ የሚችል የሰላም መሪ አለ ብዬ ጊዜየንም ጉልበቴንም የማባክንበት ምክንያት የለኝም:

አሁን ጥያቄውም ውሳኔውም በያንዳንዳችን እጅ ነው

1. በካርተር ማእከልና በእንግሊዝ ተወካይ ባንዳ በዘረኛ አምባ ገነን በባርነት፣ ገበያ ለማረጋጋት ወንዝ የሚጨምሩትን ፍርፋሪ እየጣሉልን ያውም ለመለስ ደጋፊዎች፣ የማንደግፍ ደግሞ ዉሃ፣ ውሃ እህል፣ እህል እያልን አልቀን ልጆቻችንን አገር አልባ ባሪያ አድርገን እናልፋለን?

   ወይስ

2. ነጻነታችንን አስከብረን ለልጆቻችን ነጻ ሐገርና ነጻነትን አውርሰን የሰላም እንቅልፍ እናንቀላፋለን?

መልሱ ለያንዳንዳችን

ውጭ ስለሚኖረው ወገናችን ስነ አእምሮ (mind setup} በሚቀጥለው እመለስበታለሁ

አመሰግናለሁ

# እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!

# እንፅና!